**ORIGINAL ARITICLE**

# በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለው ሚና (በ11ኛ ክፍል የፋሲለደስ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተተኳሪነት) አማራ ክልል፡ ኢትዮጵያ

ፋሲካ ውበቱ[1]ና አገኘሁ ተስፋ[2]

## አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን ሚና መመርመር ነው። የጥናቱ ንድፍ ባለሁለት ቡድን ፍተነታዊ ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በሰሜን ጎንደር ዞን በጎንደር ከተማ በፋሲለደስ መሰናዶ ትምህርት ቤት በ2009 ዓ.ም የ11ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙት 1201 ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጪ ንሞና የተመረጡ የ11ኛ K እና የ11ኛ B ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ከእነሱም በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test) ተተንትነዋል። በውጤት ትንተናው መሠረትም የሙከራው ቡድን ድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድን አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ጉልህ ልዩነት ($p = 0.0428$) አሳይቷል። በተመሳሳይ መልኩ የሙከራው ቡድን የድኅረትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድን የማንበብ ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት በልጦ ጉልህ ልዩነት ($p = 0.0206$) አሳይቷል፡፡ ከዚህም በመነሳት በትብብር መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ፍላጎት ለማሳደግ ከተለመደው ግላዊ የመማር ምርጫ የበለጠ አስተዋጽኦ አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። በጥናቱ ውጤት መሰረትም በትብብር መማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታና የማንበብ ፍላጎት ለማሳደግ ጠቃሚ መሆኑ በመፍትሄነት ተጠቁሟል።

ቁልፍ ቃላት፤ በትብብር መማር፣ አንብቦ መረዳት፣ ፍላጎት

## መግቢያ

### የጥናቱ ዳራ

በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ከሚጠቀሙባቸው የመማር ምርጫዎች መካከል ትብብራዊ፣ ውድድራዊ እና ግላዊ የሚባሉት ዘዴዎች ተጠቃሽ ናቸው። በሦስቱ የመማር ምርጫዎች የዓላማና የተግባር ልዩነት አለ። ለምሳሌ፡ - በማረው (1998) ዋቢ የተደረጉት ኦዊንስና ስትራተን (1980) በትብብር የመማር ምርጫ ተማሪዎች ግላዊ ዓላማቸውን ከግብ የሚያደርሱት ከሌሎቹ ጋር በጋራ ሲሰሩ ብቻ መሆኑን በመግለጽ፣ ትብብራዊ የመማር ምርጫ የጋራ ግብና ዓላማ እንዳለው ይገልጻሉ። ውድድራዊ በሚባለው የመማር ምርጫ ደግሞ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በርሳቸው እየተወዳደሩ በሚሰሩት ስራ የአንዱ ውድቀት ወይም ሽንፈት ለሌላው ስኬት ምክንያት እንደሚሆንና የአሸናፊው ዓላማ ከግብ እንደሚደርስ ገልጸዋል። በግላዊ የመማር ምርጫ ግላዊ ዓላማ እውን የሚሆነው እርስ በርስ በመወዳደር ወይም በትብብር በመስራት ሳይሆን እራስን ችሎ በመስራትና በግላዊ ጥረት ብቻ ነው፤ የየግላቸውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚል መነሻ የሚማሩ ተማሪዎች የየግላቸውን ስራ ከሰሩ በኋላ በዓላማው ከግብ መድረስ አለመድረስ እየተገመገሙ ለእያንዳንዱ ውጤት ይሰጣል እንጅ የአንዱ ተማሪ ስራ ከሌላው ተማሪ ስራ ጋር አይነጻጸርም በማለት ገልጸዋል (ማረው፣ 1998፤ ጆንሰን ና ጆንሰን 1994)።

እነዚህ ምሁራን የሦስቱን የመማር ምርጫዎች ዓላማና ተግባር በግልጽ ያስረዱ ቢሆንም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሻለውን የመማር ምርጫ ለማወቅ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

ቦንዌልና ኢሲዮን (2003) እና ዴቪስ (2007) እንደሚገልጹት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የመማር ማስተማሩ ሂደት ቋንቋን እንዴት እናስተምር ከሚለው መምህራንን ማዕከል ካደረገው ባህላዊ የማስተማር ዘዴ የመዋቅራዊያን (structuralism) ንድፈ ሃሳብ ተማሪዎችን ማዕከል ወደአደረገው ተማሪዎች ቋንቋን እንዴት ይማሩ? የድህረ

1 ፋሲለደስ አጠቃላይ ፪ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት፡ የአማርኛ መምህርት

2 ጎንደር ዩንቨርሲቲ፡ ሶሻል ሳይንስ እና ስነ ሰብዕ ኮሌጅ፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ፡ ፖ፡ሳ፡ቁ፡ 196፡ኢሜል፡ agetesfa@gmail.com

ዘመናዊነት (post modernism) ንድፈ ሃሰብ ተሻግሯል።

ትምህርት በማያቋርጥ ፍልስፍናዊና ተግባራዊ የለውጥ ሂደት ውስጥ ያለፈና በማለፍም ላይ የሚገኝ ነው፡፡ከፍተኛ የፍልስፍናና የተግባር መለዋወጥ አሳይተዋል ተብለው ከሚጠቀሱት አንዱ የቋንቋ ትምህርት ነው (አግራዋል፣ 1996)። በዚሁ መሰረት ተለምዷዊው የማስተማሪያ ዘዴ በየጊዜው በአዳዲስ ንድፈ ሃሳቦችና ተግባራዊ የምርምር ግኝቶች እየታረመ አሁን ካለበት ደረጃ ሊደርስ ችሏል። ይህም ጥናት ከዘመነኛ የቋንቋ ንድፈ ሃሳቦች መካከል በሰፊው ተቀባይነት እያገኘ ባለው በትብብር መማር (Cooperative Learning) ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ለትብብር መማር አስተዋጽኦ ያበረከቱ ንድፈ ሃሳቦች ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም፡- የማህበራዊ መስተጋብር፣ የአዕምሮታዊያን እና የባህርያዊያን ንድፈ ሃሳቦች ናቸው፡፡ የማህበራዊ ንድፈ ሃሳብ በዋነኛነት በባንዱራ ትውረት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ትውረቱ በትብብር የመማር ዘዴ ከሌሎች የመማር ማስተማር ሞዴሎች የተለየ መሆኑን ያረጋግጣል። ይህ ትውረት በ1920ዎቹ እና በ1930ዎቹ በሌቪን፣ በ1940ዎቹ በደች ፣ እንዲሁም በ1990ዎቹ በኮፋ ይበልጥ እየዳበረ እንደመጣ ይገለጻል (ጆንሰን ና ጆንሰን 1994) ። ንድፈ ሃሳቡ መማርን ከፉክክር ወደ ትብብር የቀየረ ነው።

የአዕምሮታዊያን ንድፈ ሃሳብ በፒያጀትና ቪጎትስኪ ትውረት ላይ የተገነባ ሲሆን የአዕምሮታዊያን ንድፈ ሃሳብ ከአዕምሮ እድገት ትውረት ያገኘው ድጋፍ በትብብር መማር ተቀባይነት እያገኘ እንዲመጣ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የአዕምሮታዊያን ንድፈ ሃሳብ ውስጣዊ መነሳሳትን ከትብብር መማር ጋር አቀናጅቶ በማቅረብ ላይ የተመሰረተ ነው። የአዕምሮ እድገት ትውረት መሰረቱ የፒያጄት (1966) እና የቪጎትስኪ (1978) ስራዎች ናቸው።

ለባህርያዊያን ንድፈ ሃሳብ ደግሞ የስኪነር (1985) ትውረት ተጠቃሽ ነው። የዚህ የነስኪነር ንድፈ ሃሳብ አራማጆች ሽልማትና ማነቃቂያ መስጠት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ጠቀሜታ እንዳለው የሚያምኑ ናቸው። ይህም በሽልማት የተበረታቱ ተግባራትን ደግመው ይፈፅማሉ ከሚል እምነት የመነጨ ሲሆን ውስጣዊ መነሳሳት ወደ ውጤታማ መማር የሚያመራ ወሳኝ ተላውጦ ነው፤የሚልን ሃሳብ የሚያራምዱ ናቸው።

በአጠቃላይ የፒያጄት ትውረት፣ መማር በተማሪው ንቁ ተሳትፎ የሚመጣ መሆኑን ትኩረት ሲሰጥ የቪጎትስኪ(1978) ትውረት ደግሞ ለመማር ማህበራዊ መስተጋብር ወሳኝ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። የስኪነር ትውረት ደግሞ ለመማር ማነቃቂያና ሽልማት ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን የሚያቀነቅንነው።

ከላይ የተገለጹት ሦስቱ ንድፈ ሃሳቦች ለትብብር መማር ዘዴ መዳበር የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ከገለጻው መረዳት ይቻላል።

ስላቪን (1995) በትብብር የመማር ሞዴል በጆንሰንና ጆንሰን (1975) እንደ ተመሰረተና በትብብር መማር ሁሉም ተማሪዎች አንድን ተመሳሳይ ተግባር በጋራ በመስራት የጋራ ግብን ለማሳካት በሚኖራቸው እምነት ላይ የሚመሰረት እንደሆነ ጠቅሰዋል።ጆንሰን፣ ጆንሰንና ሆሊዮቢክ (1986)፣ ስላቪን (1995) ሊያንግ (2002) በተለያየ አገላለጽ ያሰፈሩት ሃሳብ እንደሚያስረዳው በትብብር መማር ካለፉት አስርት አመታት ወዲህ በክፍል ውስጥ የማስተማር ሂደት አዲስ አይነት አቀራረብ በመሆን ብቅ ያለና ይህን የትምህርት አቀራረብ ዘዴ በእጅጉ ተመራጭ እንዲሆን ካደረጉት አበይት ጉዳዮች መካከል ተማሪዎች ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ፣ በከፍተኛ ሁኔታ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው ያደረገ ነው። በተጨማሪም የተማሪዎች ማህበራዊ ክህሎታቸው እንዲዳብር ማስቻሉ፣ በቡድን አባላት መካከል የሚኖረውን የፍላጎት፣ የችሎታ፣ የጾታ እና የጎሳ ወ.ዘ.ተ ልዩነትን ማጥበቡና ተማሪዎች የሚማሩበትን የትምህርት ይዘት በአግባቡ መረዳት እንዲችሉ ማድረጉ ተመራጭ የመማር ዘዴ/ ምርጫ እየሆነ እንዲመጣ አድርጎታል። በመሆኑም ዘዴው በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የትምህርት ደረጃ፣ በማንኛውም የትምህርት አይነትና በየትኛውም የእድሜ ክልል ለሚገኙ ተማሪዎች አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለ ተመራጭ የመማሪያም፣ የማስተማሪያም ዘዴ እንደሆነና በአግባቡ ከተሰራበት የተማሪዎችን ውጤት እንደሚያሳድግና ጭንቀትንም እንደሚቀንስ አክለው ያስረዳሉ።

ከነዚህ ምሁራን ሃሳብ በተጨማሪ በትብብር መማር የተማሪዎችን አቅምና የትምህርት ውጤት በማሳደግ ሂደት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት ባሳተሟቸው የምርምር ስራዎች ላይ አስፍረዋል። ለምሳሌ፡- ቢቢ (2002)፣ ካሳር (2003) እና ሀበረያን (2007), ባጠኑት ጥናት በትብብር መማርን በክፍል ውስጥ በመተግበር ማስተማር በተማሪዎች መማር ላይ አዎንታዊ ውጤት ማስመዝገቡን አረጋግጠዋል።

እንዲሁም ጆንሰንና ጆንሰን (1989) ዲህራጃ እና ኩማሪ (2013) በትብብር የመማር ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች በጥንታዊ ዘዴ ከተማሩት ጋር ሲነፃፀሩ ፅንሰ ሀሳብን በጥልቀት የመረዳት ችሎታቸው፣ የማስታወስ አቅማቸው፣

የርስበርስ ግንኙነታቸውና የትምህርት ውጤታቸው እንደተሻሻለ ገልጸዋል፡፡ ጆንሰን (2008) በበኩላቸው ማንበብን ማስተማር ብቻ ሳይሆን ማንበብን ለመማር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ለጥሩ ውጤት እንደሚያበቃና የማንበብ ተነሳሽነትንም እንደሚያሳድግ ይገልፃሉ።

በተመሳሳይ ኑናን (1989)፣ ናታል (1996 እና 2000) የተማሪዎች የተሳታፊነት ስሜት ሊጐለብት የሚችለው በፀጥታ ከሚያነቡ ወይም መምህራንን ብቻ ከሚያዳምጡ ይልቅ በክፍል ውስጥ ተግባራትን በራሳቸው ባግባቡ በመፈፀም ዕውቀትን ማግኘት ሲችሉ ነው። በዚህ ዘዴ መማር ማንበብ ለተማሪዎች የመዝናናት ስሜትን በመፍጠር እግረ መንገዳቸውን በክሂሉ ላይ ይበልጥ ፍላጐት እንዲያድርባቸው ያደርጋል፤ በማለት ገልጸዋል።

ከላይ ሃሳባቸውን ካሰፈሩት የምሁራን ሃሳብ መረዳት የሚቻለው በትብብር የመማር ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያሳድግ፤ ለተማሪዎች ሰፊ የመለማመጃ ጊዜ የሚሰጥና ንቁ ተሳትፏቸውን የሚጠይቅ፣ የመረዳዳት ሁኔታን የሚፈጥር፣ የመምህራንን ጫና የሚቀንስ፣ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂልና የማንበብ ፍላጎት የሚያሳድግና በራስ የመማር ችሎታን የሚያዳብር፣ ከሌሎች ጋር የመስራት ልምድን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ከግላዊ የመማር ምርጫ የተሻለ መሆኑን ነው።

ለማጠቃለል ተማሪዎች ቋንቋን እንዴት ይማሩ? ለሚለው የድህረ ዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ አራማጆች ጥያቄ ምሁራን ተማሪዎች ቋንቋን በቡድን (በትብብር) ቢማሩ የተሻለ መሆኑን በጥናት ውጤታቸው አሳይተዋል። ይህም ጥናት በትብብር የመማር ዘዴን ከምሁራኑ አቀራረብ አንጻር ተግባራዊ በማድረግ በአንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን የውጤት አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት ለማሳየት ይሞክራል።

## የጥናቱ መነሻ ችግር

በዚህ ርዕስ ጥናተ ለማካሄድ ከተፈለገባቸው ምክንያቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሌሎች ክሂሎች በበለጠ (በ11ኛ ክፍል መማሪያ መፅሃፍ) ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ፤ እንዲሁም በአገኘሁ (1990) ዋቢ የተደረጉት ማስተዋል (1989)፣ በየነ (1985)፣ ጌታቸው(1986)፣ ትንሳኤ 1988) እንደገለፁት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ዋነኛ ጉዳይ በመሆኑ ይህንን ትኩረት የተሰጠው አብይ ችሎታ በትብብር መማርን ተግባራዊ በማድረግ በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ የሚታየውን ለውጥ በጥናት ለማረጋገጥ መፈለግ በዋናነት የሚጠቀስ ነው። በተጨማሪም በብዙ አጥኝዎች የተለያዩ የጥናት ውጤት መቅረባቸው ማለትም አንዳንድ አጥኝዎች በትብብር መማር ከትምህርት ውጤት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ (አዎንታዊ ግንኙነት) አለው የሚል የጥናት ውጤት ሲያቀርቡ ለምሳሌ፡- ማረው(1998)፣ ስላቪን (1978)፣ ጆንሰን፣ ኔልሰንና ስኮን (1986) ተማሪዎች በጋራ ሆነው በትብብር በመስራታቸው ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ማስመዝገባቸውን ሲያረጋግጡ አንዳንዶቹ ደግሞ በትብብር መማር ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊ መሆኑን ይገልጻሉ። ለምሳሌ፡- በማረው (1998) ዋቢ የተደረጉት ክላርክና ስታር እንደሚያስረዱት፣ መማር ግላዊ ተግባር በመሆኑ ግላዊ ጥረት ብቻውን ለጥሩ ውጤት ያበቃል የሚለው ሃሳብ በሱሊቫን (1995) ጥናት አዎንታዊነቱ ተረጋግጧል። ዴቪስ (1995) እንደገለጹት የማንበብ ችሎታ ግላዊ፣ በጊዜና በቦታ የሚከናወን የአንድን ጽሁፍ መልዕክት በመረዳት ምላሽ ለመስጠት ጥረት የሚደረግበት አዕምሯዊ ተግባር ነው።በመሆኑም ንባብ ግላዊ ተግባር እንጂ ቡድናዊ አለመሆኑን ይገልጻሉ።

ከትብብራዊ ይልቅ ውድድራዊ የመማር ምርጫ የተሻለ ውጤት እንደተመዘገበበት የገለጹት ደግሞ በማረው ዋቢ የተደረጉት ቶምፕሰን (1972) ናቸው። ይህን መቋጫ ላይ ያልተደረሰበትን ጉዳይ በጥናት ማረጋገጥ ሌላው ለጥናት ያነሳሳ ምክንያት ነው። የሃገራችን ምሁራን ጥናቶች ትኩረት  በትብብር መማር የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆናቸውም ሌላው ለጥናቱ ያነሳሳ ምክንያት ነው። ለምሳሌ ፡- ሙላት (2007) የመምህራን የቡድን ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፣ ሄዋን (2007) በትብብር የመማር የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ ጥናት ያደረጉ ሲሆን፤ ግርማ (2003) የግንዛቤ ዕጥረት መኖር የእንግሊዝኛ ቋንቋን በቡድን ተኮር ዘዴ ለማስተማር ያለው ተጽዕኖ በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል።

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የዚህ ጥናት መነሻ ከመሆኑም በላይ በትምህርት ሂደት ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ እያለ በቀደምት አገርኛ ጥናቶች አለመዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዩን ተመራጭ አድርጓታል። በተጨማሪም  በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃና በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የተገኘ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምድና ከሌሎች የቋንቋ መምህራን ጋር ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ በመወያየት የተገኘ  ልምድ ብዙ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር እንዳለባቸውና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመመዘን በሚሰጣቸው የማጠቃለያ ፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ መቻሉም በዚህ ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ሌላው መነሻ ሆኗል። ተማሪዎችም በአንብቦ መረዳት ትምህርት ወቅት በማንበብ ክሂሉ ላይ በአግባቡ ከመሳተፍ፣ ክትትል ከማድረግና በትምህርቱ ከመሳብ ይልቅ በወሬ የመጠመድና

የመሰላቸት ስሜት ሲያሳዩ ማስተዋልም ምናልባት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆነውና ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ፍላጎት የሌላቸው ከአቀራረብ ዘዴው ጋር የተያያዘ ችግር ይሆን? የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሳ በጉዳዩ ላይ ጥናት ለማካሄድ አነሳስቷል። በመሆኑም የዚህ ጥናት ዓላማ በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን ሚና መመርመር ይሆናል።

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ፍትነታዊ የምርምር ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ሲሆን የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ ፈተና ንድፍን ተግባራዊ አድርጓል። ተላውጠዎችን በተመለከተ በትብብር መማር ነጻ ተላውጦ ሲሆን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ፍላጎት ጥገኛ ተላውጦዎች ናቸው።

## የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

የዚህ ጥናት መልክዓ ምድራዊ ወሰን በጎንደር ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኘው የፋሲለደስ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ሲሆን፤ በ11ኛ ክፍል ብቻ የተገደበ ነው። ከይዘት አንጻርም ናታልና (1996) እና ሲልቨርስቴይን (1994) ከአንድ ቴክስት ውስጥ ሊዘጋጁ የሚችሉ ስድስት ዋናዋና የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መካከል ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው የተመረጡት ሦስቱ ናቸው። እነዚህ የመልመጃ አይነቶች የተመረጡበት ምክንያት ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሃፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ነው።

በጎንደር ከተማ አስተዳደር ስድስት የመሰናዶ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከነዚህ መካከል የፋሲለደስ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በአመቺ የንሞና ስልት ተመርጧል። አመቺ ንሞና ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያትም የዚህ ጥናት መነሻ ሃሳብ በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን ሚና ለማረጋገጥ በሙከራ የሚሰራ እንደመሆኑ ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ሰፊ ክፍለ ጊዜ ለማግኘት አመቺ የጥናት አካባቢና ትምህርት ቤት መምረጥ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። የአመቺ ንሞና ዘዴ ለተጠኝዎች እኩል እድል የማይሰጥ ቢሆንም ጥናቱን በአግባቡ ለማካሄድ ከአምስት ሳምንታት በላይ በማስፈለጉ እና ትምህርቱን በታቀደው ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ትምህርት ቤት በማስፈለጉ የንሞና ስልቱ ተመርጧል።

በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች በ2009 ዓመተ ምህረት በፋሲለደስ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ21 የመማሪያ ክፍሎች ተደልድለው ከሚማሩት 1201 የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ሲሆን በአንድ ክፍል በአማካይ 50 ተማሪዎች ይማራሉ። ይህ ጥናት በሙከራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉንም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ አስቸጋሪ ነው። ከዚህ የተነሳ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን ቁጥር ውስን ማድረግ ተገቢ ነው። ስለሆነም አጠቃላይ የጥናቱ አካላይ የሆኑትን 21 የመማሪያ ክፍሎች ዕጣ ውስጥ በማስገባት በእድል ሰጭ የንሞና አመራረጥ ዘዴ የ11ኛB እና የ11ኛK ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ተደርጓል። ዘዴው የተመረጠበትም ለተማሪዎች እኩል እድል ስለሚሰጥና የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ እንዲሆን ስለሚያደርግ ነው።

## የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓብይ ዓላማ ከግምት ውስጥ በማስገባት አግባብነት አላቸው ተብለው የተመረጡትየመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው። በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት መርሃ ትምህርቱንና መማሪያ መጽሃፉን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና በተግባር ላይ ውሏል። ቅድመ ፈተናው የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ለመለካት የተዘጋጀ ሲሆን ፈተናው ለጥናቱ ተሳታፊዎች ከመሰጠቱ በፊት በሁለት ሁለተኛ ዲግሪና በአንድ ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው የቋንቋው መምህራን እና ሌሎች የፈተና ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበትና በጥናቱ በማይካተቱ 30 የ11ኛJ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራ (pilot test) ተደርጎበት ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። ድህረ ፈተናውም ከቅድመ ፈተናው ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን በተለያየ ስልት የተማሩ ቡድኖች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ምን ያህል እንደሆነ መረጃ የሚሰጥ ነው። ይህም መርሃ ትምህርቱንና የመልመጃ አይነቶችን መሰረት አድርጎ ተዘጋጅቷል። ፈተናው ለተሳታፊዎች ከመሰጠቱ በፊት በሦስት የቋንቋ ምሁራን እንዲገመገም ተደርጎ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል።

የጽሁፍ መጠይቅ የዚህ ጥናት ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በተለያየ በትብብር መማር ስልቶች የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ከመማራቸው በፊትና ከተማሩ በኋላ ያላቸውን የማንበብ

ፍላጎት ለማነጻጸር በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገለግሏል። የጽሁፍ መጠይቁ በጀንሰን (2008) ፍላጎትን ለመለካት ከተዘጋጁ የመጠይቅ ጥያቄዎች ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ ተሸሽለው የተወሰዱ ሲሆን መጠይቁ ለተሳታፊ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት መምህራንና ሦስተኛ ዲግሪ ባለው አንድ መምህር እንዲገመገም ተደርጓል። በተጨማሪም የጽሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለመለካት የጥናቱ ተሳታፊዎች ባልሆኑ 30 የ11ኛJ ክፍል ተማሪዎች ላይ የቅድመ ሙከራ ጥናት ተካሂዶበት ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል።

በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ለማንበብ ያላቸውን ፍላጎት እንዲገልጹ በማድረግ ላይ ያተኮሩ ናቸው። የጥያቄዎቹ አይነት ዝግ ሲሆን በሬቲንግ ስኬል የተዘጋጁ መጠን አመልካች ጥያቄዎች ናቸው። የጥያቄዎቹ ብዛት አስራ ሁለት ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ በጣም እስማማለሁ (4) ፣ እስማማለሁ (3) ፣አልስማማም (2) እና በጣም አልስማማም (1) የሚሉ አማራጮች ተሰጥተዋል።

### የመረጃ አተናተን

በጥናቱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በተመረጡት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኘውን መረጃ ለመተንተን ነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስታትስቲካዊ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። የትንተናው ስልት መጠናዊ (quantitative) በመሆኑ SPSS የመረጃ መተንተኛ ሶፍትዌር አገልግሎት ላይ ውሏል።

## የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### የውጤት ትንተና

ጥናቱ እንዲመልሳቸው የታሰቡ ጥያቄዎች በትብብር መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ከተለመደው (ግላዊ መማር) የተለየ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው? እና በትብብር መማር የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ከተለመደው (ግላዊ መማር) የተለየ ድርሻ አለው? የሚሉ ናቸው። ጥያቄዎችንም ለመመለስ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል። በትብብር መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ከተለመደው (ግላዊ መማር) የተለየ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በተሰጡት ፈተናዎች መረጃው ተሰብስቦ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ተግባር ላይ ውሏል። ውጤቱም በሰንጠረዥ 1 እና በሰንጠረዥ 2 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 1 ፡-የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተለዋዋጭ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት | 40 | 53.7 | 14.7 | 2.407 | 75 | 0.0692 |
| የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት | 37 | 56.7 | 15.8 | | | |

በሰንጠረዥ 1 የቀረበው መረጃ የጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ውጤት የሚያሳየው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት አለመኖሩን ያረጋግጣል፤ (ቲ (75=ፒ>0.05) የ ፒ ዋጋ 0.0692 ከመቁረጫ ነጥቡ በልጦ ተገኝቷል። ይህ የሚያመለክተው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት አለመኖሩን ነው።

ሰንጠረዥ 2፡- የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት

| ተለዋዋጭ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን ድህረትምህርት | 40 | 63.9 | 11.06 | 2.385 | 75 | 0.0428 |
| የቁጥጥር ቡድን ድህረትምህርት | 37 | 56.9 | 13.99 | | | |

በሰንጠረዥ 2 እንደተመለከተው ምናልባትም ስህተት 5% (ፒ<0.05) በመተው ወይም 95% እርግጠኛ በመሆን በተሰራው ስሌት የነጻ ናሙና ፍተሻ ውጤት የሚያሳየው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት መኖሩን ነው (ቲ(75=2.385 ፒ<0.05)። ይህም የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ የተለያየ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው መሆኑን ከማሳየቱም ባሻገር የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት የአንብቦ መረዳት ችሎታ (63.9) ከቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታ (56.9) የበለጠ መሆኑን ያሳያል። የዚህም ምክንያቱ ተማሪዎች በትብብር መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አበርክቶላቸው ሊሆን ይችላል። በትንተናዉ ውጤት መሠረትም በትብብር መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ሚና አለውን?" የሚለው የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ማግኘቱን ከመረጃው ማረጋገጥ ይቻላል።

ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ በትብብር መማር የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ከተለመደው (ግላዊ መማር) የተለየ ድርሻ አለው? የሚል ነው። ለዚህም የሙከራውና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የማንበብ ፍላጎታቸውን የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ ተጠይቀዋል። የተገኘው መረጃም በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test) ቀመር ተሰልቷል። ውጤቱም በሠንጠረዥ.3 ተመልክቷል።

ከሰንጠረዥ 3. መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አማካይ ውጤቶቹ በንፅፅር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ተቀራራቢ መሆኑን በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን የነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል። በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድኖች የቅድመትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል። መረጃው በነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ሲሰላ(ቲ(75)=.981 p=0.0616) ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 በልጦ በመገኘቱ በሁለቱም ቡድኖች የቅድመትምህርት የማንበብ ፍላጎት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ አሳይቷል።

ሠንጠረዥ 3. የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርት የማንበብ ፍላጎት በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት ቀመር

| ተለዋዋጭ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራቡድንቅድመ ትምህርት | 40 | 2.28 | 0.29162 | 0.981 | 75 | 0.0616 |
| የቁጥጥር ቡድንቅድመ ትምህርት | 37 | 2.34 | 0.29648 | | | |

በሠንጠረዥ4. የቀረበዉ መረጃ እንደሚያሳየው ደግሞ በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። ውጤቱ በ75 የነጻነት ደረጃ (ቲ 3.38፣ p<0.05) የ ፒ ዋጋ 0.020 ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 አንሶ ተገኝቷል። ይህም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች ከተማሩ በኋላ በማንበብ ፍላጎታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት እንደታየባቸው ያመለክታል። ከዚህም በትብብር የመማር ምርጫ ከተለመደው ግላዊ የመማር ምርጫ በበለጠ ሁኔታ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 4. የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት የማንበብ ፍላጎት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር

| ተለዋዋጭ | የተሳታፊች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 40 | 2.7 | 0.46 | 3.38 | 75 | 0.0206 |
| የቁጥጥር ቡድን | 37 | 2.37 | 0.38 | | | |

በትንተናው ውጤት መሠረትም በትብብር መማር የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት በማሳደግ ረገድ ሚና አለውን?" የሚለው የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ማግኘቱን ከመረጃው ማረጋገጥ ይቻላል።

የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በትብብር መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ጉልህ ሚና እንዳለው በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን የስታቲስቲክስ ቀመሩ

(ፒ< 0.05) ያሳያል። የማንበብ ፍላጎታቸውንም በተመለከተ በትብብር መማር ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው በትንተናው የተገኘው ውጤት አመላክቷል። በዚህም በቅድመና በድህረ ትምህርት የማንበብ ፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት (ፒ< 0.05) ታይቷል።

በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትብብር መማርን በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት ቢጠቀሙ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ እንዲሁም ፍላጎት ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል ጥናቱ ያሳያል።

## የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በትብብር መማር አንብቦ በመረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለውን ሚና መመርመር ላይ ነበር። በመሆኑም በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች በትብብር መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን ፋይዳ እንዲሁም በትብብር መማር በማንበብ ፍላጎት ላይ ያሳየው መሻሻል መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተተንትነዋል። እነዚህን ዓላማዎች ለማረጋገጥ ጥናቱ መረጃዎችን በመተንተን ረገድ በቅድሚያ ያየው የሙከራ ቡድኑንና የቁጥጥር ቡድኑን ቅድመ ትምህርት የነበራቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለካት ነው። በዚህም መሰረት የሙከራናየቁጥጥር ቡድኖቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተፈትሿል፡፡ ከነጻ ናሙናቲ-ቴስቱ የተገኘው ውጤት የተጠኝ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ተመሳሳይ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው መሆኑን በ75 የነጻነት ደረጃ (ቲ= -2407፣ፒ>0.05) አሳይቷል። የፒዋጋ 0.0692 ከመቁረጫ ነጥቡ በልጦ በመገኘቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ቅድመትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል።

ቀጥሎም የሁለቱ ቡድኖች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድህረትምህርት ልዩነት መኖሩና አለመኖሩ ተለይቷል፡፡ በዚህም መሰረት ድህረትምህርት በትብብር መማር ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን የፒዋጋ 0.0428 ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 አንሶ፣በ75 የነጻነትደረጃ (ቲ = -2.385፣ፒ< 0.05) አመልክቷል። ይህም በሁለቱ ቡድኖች ድህረትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያስረዳል። በመሆኑም በትብብር መማር የተማሪዎችንአንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና የጎላ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

ይህም ውጤት ከማረው (1998)፣ ከጆንሰን፣ ከቢቢ (2002)፣ ከካሳር (2003)፣ ከሃበርያን (2007) የጥናት ውጤቶች ጋር ይደጋገፋል። በተመሳሳይ ከስቴቨንና ስላቪን (2000)፣ ከሪቻርድሰንና ሌሎች (2006)፣ ከላርሰን ፍሪማን (2000) ድምዳሜ ሀሳብ ጋር ስምሙ ሆኖ ተገኝቷል። ዘዴው በክሂሉ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለውና በዘዴውና በማንበብ ክሂሉ መካከል ተዛምዶ አለው ካሉት ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

በሌላ በኩል ከትብብራዊ የመማር ምርጫ ግላዊ የመማር ምርጫ ከትምህርት ውጤት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ መኖሩን ካረጋገጡት የሱሊቫን (1995) ጥናትና በማረው (1998) ዋቢ የተደረጉት ክላርክና ስታር ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ይቃረናል። ሆኖም እንደሱሊቫን፣ክላርክና ስታር ድምዳሜ ቢሆን በዚህ ጥናት ተሳታፊ የሆኑት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ላይ ከቅድመ ፈተናው የበለጠና የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ በቻሉ ነበር።

መደበኛ ልይይቱንም በተመለከተ ከቅድመ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ይልቅ የድህረ ትምህርቱ የመደበኛ ልይይት ውጤት አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር ተማሪዎቹ አንብቦ መረዳትን በትብብር መማራቸው የማንበብ ችሎታቸውን እንዳሻሻለውና በተማሪዎቹ መካከልም የችሎታ መቀራረብን እንደፈጠረላቸው ያመላክታል።

በዚህ ጥናት ውጤት አንብቦ በመረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በመተባበር በመማራቸው ያነበቡትንና የተረዱትን ሃሳብ እርስ በርስ በመወያየታቸው ለቀረበው ምንባብ አውዳዊ ፍቺ መስጠት፣ ሃሳቦችን በራስ አገላለጽ መግለጽና የራስ አስተያየትን መስጠት በሚያስችል መልኩ መቅረባቸውና ቀላልና ግልጽ በመሆናቸው ጭምር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መሻሻል ችሏል ቢባል ተቀባይነት ይኖረዋል።

ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ የሚያነሳው በትብብር መማር በማንበብ ፍላጎት ላይ የሚያሳየው መሻሻል መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ሲሆን በዚህም በኩል በሠንጠረዥ3. እንደቀረበው የድህረ ትምህርት የማንበብ ፍላጎት ከቅድመ ትምህርት በልጦ ታይቷል። የማንበብ ፍላጎት የመደበኛ ልይይቱም ከቅድመ ትምህርት ይልቅ በድህረ ትምህርቱ አንሶ መገኘቱ ተማሪዎች በትብብር አንብቦ የመረዳት ክሂልን ከመማራቸው በፊት የማንበብ ፍላጎታቸውን ሊያነሳሱ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳልተመቻቹላቸው ያሳያል።

አማካይ ውጤታቸውም ሲነጻጸር የድህረ ትምህርት ፍላጎት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፍላጎት በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት (ፒ< 0.05) አሳይቷል፡፡ በመሆኑም በትብብር መማር በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ላይ ያሳየውን መሻሻል ያመላከተው የዚህ ጥናት ውጤት ስላቪን (1995)፣ ጆንሰንና ጆንሰን (1994)፣ኑናን (1989) ከደረሱበት የድምዳሜ ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው። በትብብር መማር የማንበብ ፍላጎትን ይጨምራል፤ የማንበብ ችሎታን ያዳብራል በሚል የደረሱበት ድምዳሜ በትብብር መማር የማንበብ ችሎታን ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽኦ ያሳያል። ይህም ለተሳታፊ ተማሪዎች በማስተማሪያነት የቀረቡ አሀዶች ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደረጉ በመሆናቸው ነው የሚል አንድምታ ይኖረዋል።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት በትብብር መማር የማንበብ ችሎታን የማጎልበትና የማንበብ ፍላጎትን የማሳደግ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል። ለዚህም ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ቀመር መሰረት በልጦ መገኘቱና የድህረ ንባብ ፍላጎት ከቅድመ ንባብ ፍላጎት አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መገኘቱ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። በጥቅሉ በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች ያመላከቱት በትብብር የመማር ምርጫን በተገቢው መንገድ ተጠቅሞ ማስተማር የማንበብ/ አንብቦ የመረዳት ችሎታንና የመማር ፍላጎትን ከማጎልበት አንጻር ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ነው።

## ማጠቃለያ፣መደምደሚያ ና የመፍትሄ ሃሳብ

### ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በትብብር መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታንና ፍላጎትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው። በዚህም መሰረት ጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች በትብብር መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ከተለመደው (ግላዊ መማር) የተለየ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው? እና በትብብር መማር የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት በማሻሻል ረገድ ከተለመደው(ግላዊ መማር) የተለየ ድርሻ አለው? የሚሉት ናቸው።

የጥናቱ ተሳታፊዎች በሰሜን ጎንደር ዞን በጎንደር ከተማ በፋሲለደስ መሰናዶ ትምህርት ቤት በ2009 ዓ.ም የ11ኛ ክፍል ትምህርታቸውን የሚከታተሉ 1201 ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች በ21 የመማሪያ ክፍሎች የተደለደሉ ሲሆን በእድል ሰጪ ንሞና የ11ኛ K እና የ11ኛ B ክፍል ተማሪዎች ተመርጠው የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል። በጥናቱ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም ፈተና ሲሆን የክፍል ደረጃውን መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፉን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሆኗል። ተሳታፊዎችም በትብብር ከመማራቸው በፊት የቅድመ ትምህርት ፈተናው እንዲሁም ቅድመ የማንበብ ፍላጎታቸውን ለመለካት ደግሞ የጽሁፍ መጠይቁ በተለያዩ ባለሙያዎች ማስተካከያ ታክሎበት በሙከራ ጥናት ተፈትሾ አስተማማኝ ሆኖ በመገኘቱ ፈተናውና የጽሁፍ መጠይቁ በቅደም ተከተል የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታና ፍላጎት ለመለካት ተግባራዊ ሆነዋል። በአጠቃላይ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትነዋል።

ከዚያም ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ቴክስቶች ለአራት ሳምንታት ሲማሩ ቆይተዋል። ከትምህርቱ በኋላም ከቅድመ ትምህርቱ ፈተና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ ተሰብስቧል። ቀጥሎም ድህረ የማንበብ ፍላጎታቸውን ለመለካትና ለማነጻጸርም የጽሁፍ መጠይቁን ሞልተዋል። የጽሁፍ መጠይቁ አስራ ሁለት ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ጆንሰን (2008) አንብቦ የመረዳት ፍላጎትን ለመለካት የተጠቀሙበትን ለጥናቱ በሚያመች መልኩ በማሻሻል ለንባብ ያላቸውን ፍላጎት እንዲለካ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል።

በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተናውና የጽሁፍ መጠይቁ ጋር አቻ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ተግባራዊ በማድረግና ውጤቱን በመረጃነት በመመዝገብ በመጀመሪያ በትብብር መማር የማንበብ ችሎታን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል። በዚህም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ (ፒ< 0.05) ጉልህ ልዩነት በመታየቱ በትብብር መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን እንደሚያጎለብት ለመረዳት ተችሏል።

በሁለተኛ ደረጃ የተነሳው መሰረታዊ ጥያቄ በትብብር መማር በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ላይ ያለው ፋይዳ ምንድነው? የሚል ነበር። በቅድመና ድህረ ትምህርት የፍላጎት መረጃው መሰረት በተሳታፊዎች የቅድመና ድህረ ትምህርት አማካዮች መካከል በስታቲስቲክስ (ፒ< 0.05) ጉልህ ልዩነት ታይቷል። በዚህም በትብብር መማር በተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ላይ ያሳየው መሻሻል መኖሩን ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና ውጤት የማንበብ ችሎታን ለማጎልበትና የማንበብ ፍላጎትን ለማሳደግ ለተማሪዎች የሚቀርቡት አሀዶች በትብብር ለመማር በሚያስችሉ ስልቶች ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል አመላክቷል። ትምህርቱም የማንበብ ፍላጎትን በሚያነሳሳ መልኩ ለተማሪዎች ቢቀርብ የማንበብ ችሎታቸው ሊጎለብት እንደሚችል ውጤቱ ጠቁሟል።

## መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል፡፡

- በትብብር የመማር ምርጫና በማንበብ ችሎታ መካከል ግንኙነት አለ። ይህም በትብብር መማር የማንበብ ችሎታን በማዳበር ረገድ ሚና አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል።
- በትብብር መማርና በማንበብ ፍላጎት መካከል ተደጋጋፊነት አለ። ይህም በትብብር መማር የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት በማነሳሳት ረገድ ሚና እንዳለው ያመላክታል።

## የመፍትሄ ሀሳቦች

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታም ሆነ የማንበብ ፍላጎት ለማሳደግ ይቻል ዘንድ የሚከተሉት መፍትሄዎች ተሰንዝረዋል።

1. በትብብር መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት መምህራን ተገንዝበው የትብብር መማርን ጠቀሜታ ለተማሪዎች ቢያስተዋውቁና ቢያስተምሩ፤ ተማሪዎችም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በትብብር እንዲሰሩ ቢደረግ።
2. በትብብር መማር የማንበብ ፍላጎትን በማጎልበት ረገድ ፋይዳው የጎላ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል። በዚህም መሰረት በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚካተቱ መልመጃዎች በትብብር መማርን የሚያበረታቱ ሆነው ቢዘጋጁ።
3. በዚህ የጥናት ውጤት ላይ ተመስርተው ሌሎች ተለዋዋጮችን ያካተተ ጥናት ወደፊት በመምህራንም ሆነ በሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ቢካሄድ ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክሂል መጎልበት የጎላ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

## ዋቢ መጻህፍት


ሄዋን እጅጉ። (2007)። "በትብብር የማስተማር ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገበበር ቅኝት"፡፡ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ማረው ዓለሙ. (1998). የመማር ምርጫና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ. *The Ethiopian Journal of Education*, 18(1), 56-68.

አገኘሁ ተስፋ። (1990)። "አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን አፈታተን የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት; በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተናዎች። "አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃፕሮግራም ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

Aggrawal, C. (1996). *Principles, Methods and Techniques of Teaching*. Vikas Publishing house pvt. Litd. New Delhi.

Bibi, A. (2002). *The comparative effectiveness of teaching English grammar with the help of textbook and using group work activities* (Doctoral dissertation, Allama Iqbal Open University, Islamabad).

Bonwell, C. C., & Eison, J. A. (2003). *Active Learning: Creating Excitement in the Class room.2003 ASHE-ERIC Higher Education Reports*. ERIC Clearinghouse on Higher Education, The George Washington University, One Dupont Circle, Suite 630, Washington, DC 20036-1183.

Davies, F. (1995). *Introducing Reading*. Cambrige: Cambrige University Press.

Dheeraj.D Kumari.R. (2013). *Effect of Co-operative Learning on Achievement in Environmental Science of School Student.* Magadh University Bodhgaya.

Girma Gezahegn (2003). In-Service En6glish Language Teacer's perception of the Factor that Influence the Implementation of Group Work Activities in ELT Classes.

*Ethiopian jornal of education.* 23(2). 103-125.
Haberyan, A. (2007). Team-based learning in an industrial/organizational psychology course. *North American Journal of Psychology*, 9(1), 143.
Johnson, D. W., Johnson, R. T (1989).Cooperation and competition: Theory and research. Edina, Minn. Interaction Book Company.
Johnson, D. W., Johnson, R. T (1994).Cooperative learning in the classroom. Alexandria, VA: Association for Supervision and Curriculum Development.
Johnson, D. W., Johnson, R. T., & Holubec, E. J. (1986). Circles of Learning: Cooperation in the Classroom (Edina, MN: Interaction Book). *Google Scholar.*
Johnson, D.W. (2008). An educational success story: Social interdependence theory and cooperative learning. *Educational Researcher*, 38(5), 365-379
Kosar, R. (2003). An experimental study on effects of cooperative learning on social studies achievement among 7th class students. Unpublished MA dissertation. PAF college of Education for Women, Rawalpindi.
Liang, T. (2002). Implementing cooperative learning in EFL teaching: Process and effects (Unpublished master's thesis). *National Taiwan Normal University*, Taipei, Taiwan.
Mulat Adane. (2007). An Exploration of Teachers Roles in Implementing Group Work with particular Reference Debre Berhan College of Teachers Education. MA thesis (unpublished). Addis Ababa.
Nunan, D. (1989). *Language teaching methodology* (Vol. 192). New York: prentice hall.
Nuttall, C. (1996). Teaching reading skills in a foreign language. Heinemann, 361 Hanover Street, Portsmouth, NH 03801-3912.
Nuttall, C. (2000).Teaching Reading Skill for in a Foreign Language (2nd ed.).London: Henemann Educational Books.
Piaget, J. (1966).Psychology of intelligence .Totowa, NJ: Littelfield, Adam
Silberstein.S. (1994). Techniques and Resource in Teaching Reading. Oxford: Oup.
Slavin, R. E. (1995). Research on cooperative learning: Consensus and controversy. *Educational leadership*, 47(4), 52-54.
Smith, F. (1971). Understanding Reading. New York, NY: Holt, Rinehart and Winston.
Vygotsky, L. S. (1978). *Mind in society* (M. Cole, V. John-Steiner, S. Scribner, & E. Souberman, Eds.).